# የውጭ ኃይሎች ተላላኪዎች የሕዝብን ጥያቄ ሊመልሱ አይችሉም!

**ኢብሳ ነመራ** 01-06-17

የኢትዮጵያ ህዝብ የሰላምን ዋጋና እጦት ጉዳት ከተሞክሮ ያውቀዋል። በተለይ ከ1960ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ የኖሩ የአሁን ጎልማሶችና አዛውንት ኢትዮጵያውያን የሰላም እጦትን አስከፊነት ቀምሰውታል። የወታደራዊው ደርግ መንግስት በህዝብ ትግል የተገኘውን የ1966 ድል ነጥቆ በኢትዮጵያውያን ላይ ተጭኖ ለኖረው ብሄራዊና ኢኮኖሚያዊ ጭቆና ምላሽ አልሰጥ በማለቱ፣ እንዲሁም ሰላማዊ ትግል የሚደረግበትን ፖለቲካዊ መብት፤ ሃሳብንና አመለካከትን የመግለጽና የሌሎችን የመቀበል፤ የፈቀዱትን አመለካከት የመያዝና የማራመድ፤ የመደራጀት፤ በግልና በቡድን ለፖለቲካ ስልጣን የመወዳደር፤ በህዝብ ድምጽ በሚገኝ ውክልና ለመንግስት ስልጣን የመብቃት መብትንና ነጻነትን አፍኖ የህዝብ የስልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት ሊረጋገጥ የሚችልበትን አማራጭ በመዝጋቱ ህዝብ የሃይል ትግል ውስጥ እንዲገባ አስገድዶት እንደነበረ ይታወሳል።

በዚህም ምክንያት፤ በ50ዎቹ ገደማ የተጀመረው የኤርትራ ህዝብ የነጻነት ጥያቄ ትግል ደርግ የህዝብን ድል ቀምቶ ስልጣን ላይ በወጣበት 1967 ዓ.ም ከመቼውም ጊዜ በላይ ተፋፋመ። በመሃል አገር ቀደም ሲል በውጭ አገር ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲን (ኢህአፓ) የመሳሰሉ የፖለቲካ ቡድኖች *ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም!* የሚል የነጻነት ትግል ማካሄድ ጀመሩ። በአመዛኙ ከመሳፍንቱ ወገን በነበሩ ሰዎች የሚመራው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህብረትም (ኢድህ) በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የትጥቅ ትግል ማድረግ ጀመረ። በተለይ ለዘመናት በህዝብ ላይ ተጭኖ የኖረው ብሄራዊ ጭቆና መፍትሄ ማጣቱ በቆጫቸው ወጣቶቸ ተደራጅቶ አርሶ አደሩን በማሰለፍ ትግል የጀመረው ህወሃት፣ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) እና ሌሎችም በአሰራዎቹ የሚቆጠሩ ብሄራዊ የነጻነት ንቅናቄዎች ደርግ የዘውዳዊውን ስርአት ብሄራዊ ጭቆና ለማስቀጠል በመወሰኑ የተፈጠሩ የነጻነት እንቅስቃሴዎች ናቸው። የእነዚህ ቡድኖች የትግል ስልት አንዱ ከሌላው የሚለይ እንዲሁም የህዝብን የበላይነት ያረጋገጠ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት የሚከተሉት መስመርና ቁርጠኝነት አንዱ ከሌላው የሚለይ ቢሆንም፣ ሁሉም ጭቆና የወለዳቸው ናቸው ማለት ይቻላል። በተለይ ሃሳብን የመግለጽ፣ የማራመድ፣ የመደራጀትና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የማድረግ፣ ለፖለቲካ ስልጣን መፎካከር የሚችሉበት የዴሞክራሲ መንገድ መከርቸሙ ወደትጥቅ ትግል እንዲገቡ ያስገደዳቸው ናቸው። ይህ ዴሞክራሲያዊ መንገድ ባይከረቸም ኖሮ በህዝብ ስለሚዳኙ ለህዝብ የበላይነት ያላቸው ቁርጠኝነት በይፋ ይፈተን ነበር።

ያም ሆነ ይህ፤ ወታደራዊው ደርግ ለህዝብ የመብትና የነጻነት ጥያቄ ሰላማዊ ምላሽ ለመስጠት ባለመፍቀዱ በተቀጣጠለው የነጻነት ትግል በመላ አገሪቱ ሰላም ደፍርሷል። በተለይ ከ1968 አጋማሽ እስከ 1970 በነበሩት ዓመታት አዲስ አበባን ጨምሮ ሁሉም የአገሪቱ ከተሞች የፍልሚያ ሜዳ ሆነው ነበር። ወታደራዊው ደርግ ከኃይል ትግል ውጭ አማራጭ አጥተው የሚፋለሙትን በአብዛኛው ወጣት ታጋዮች በገፍ ይገድል ነበር። በዚህ ወቅት የአገሪቱ ከተሞች አደባባዮች ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በዘፈቀደ የተገደሉ ወጣቶቸ አስከሬን ለመቀጣጫነት ቀኑን ሙሉ ተሰጥቶ እንዲውልባቸው ይደረግ ነበር። ምዕመናን የሚሳለሙባቸው የቤተክርስቲያን ደጃፎችን ጨምሮ ሰው የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ሁሉ የአስከሬን ማስጫ ተደርገው ነበር። ክቡሩ የሰው ልጅ አስከሬኑ እንደእንስሳ ሜዳ ላይ ጸሃይ ሲያንቃቃው መመልከት እጅግ ዘግናኝና አሳዛኝ ትእይንት ነበር። በዚህ ሁኔታ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ህይወታቸውን አጥተዋል።

በዚህ ወቅት የእያንዳንዱ ዜጋ ህይወት ወታደራዊው ደርግ ከላይ እስከ ቀበሌ በዘረጋው መዋቅር ውስጥ ባስቀመጣቸውና ያለማንም ተቆጣጣሪ የማሰር፣ አካላቸው እስኪጎድል የመደብደብ፣ የመግደል ወዘተ. ስልጣን በተሰጣቸው ሰዎች መዳፍ ውስጥ ነበረ። ምንም የማያውቁና የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ያልነበሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች እንደወጡ ቀርተዋል። ዜጎች ለማንኛውም ጉዳይ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አይችሉም። በገዛ አገራቸው በየቦታው የይለፍ ፈቃድ ይጠየቃሉ። ማምረት፣ መነገድ፣ ማህበራዊ ጉዳዮችን ማከናወን ወዘተ. አደጋ ነበረው። ዜጎች ደክመው ያፈሩትን ሃብት ያለምንም ምክንያት በአፈና ስርአቱ ባለሟሎች ተነጥቀዋል። ሴቶች ባላቸው ታስሮ ተደፍረዋል። ይህ በአጭሩ ልገልጸው የሞከርኩት እውነታ የኢትዮጵያ ህዝብ ያለፈበትን የሰላም እጦት ተሞክሮ የሚያሳይ አንዱ ክስተት ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ በ1969 ዓ/ም አጋማሽ ላይ የሶማሊያው የዚያድ ባሬ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ፈጽሞ ነበር። በወቅቱ በቂ ዝግጅት አድርጎ ወደወረራ የገባው የዚያድ ባሬ መንግስት ጦር ኃይል በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ድንበር ተሻግሮ በብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች ዘልቆ ገብቶ ነበር። ወረራው በምስራቅ እስከ ድሬዳዋ ጥግ፣ በደቡብ ምስራቅ ደግሞ በባሌ በኩል ጊንዲርና ጎሮ ከተማዎች ስር ደርሶ እንደነበረ ይታወሳል።

ታዲያ በዚያድ ባሬ ኃይል በተያዙ አካባቢዎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በወራሪው ኃይል ዘግናኝ ጭፍጨፋ ተፈጽሞባቸዋል። ህጻናት ያለአሳዳጊ ቀርተዋል። ዜጎች እድሜ ልካቸውን ሰርተው ያፈሩት ሃብት መና ቀርቷል። የመኖሪያ ቤታቸው ወድሟል። ለስደት ተዳርገዋል። በወራሪው ኃይል ተይዘው በሶማሊያ እስር ቤቶች ለዓመታት የተንገላቱትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። በዚህ ለአንድ ዓመት ያህል በተካሄደ ጦርነት የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ በምስራቅና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የማይረሳ አስከፊ የህይወት አጋጣሚ አሳልፈዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ በኋላም ሰላም አላገኘም። በሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መብትና ነጻነታቸውን ማረጋገጥ ያልቻሉ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ኤርትራን ጨምሮ በየአካባቢው የሚያካሂዱትን የነጻነት ትግል ለማፈን የወታደራዊው ደርግ መንግስት በሚወስደው እርምጃ፣ በቀጥታ የነጻነት ትግል ላይ ከሚሳተፉ ታጋዮች በተጨማሪ በርካታ ንጹሃን ዜጎች ካለፍርድ ቤት ትእዛዝና ውሳኔ ታስረዋል። ተደብድበዋል። አካላቸው ጎድሏል። ተገድለዋል። በህይወት ውለው ለማደራቸው፣ ለመሰንበታቸው፣ ለመክረማቸው ዋስትና አጥተዋል። ወጣቶች ስርአቱ የነጻነት ጥያቄን ለማፈን በሚያካሂደው ጦርነት ውስጥ እንዲሳተፉ በግዳጅ ይመለመሉ ነበር። በዚህ ሁኔታ የዜጎች የመስራት፣ ሰርቶ የመክበር፣ ወልዶ አሳድጎ ለማእረግ የማብቃት ወዘተ. እጣ ፈንታ በወታደራዊው ደርግ ባለስልጣኖች እጅ የነበረ ጉዳይ ነው።

አሁን ኢትዮጵያ ረጅም የሰላም ጊዜ አሳልፋለች። በተለይ በ1990 ግንቦት ላይ የተፈጸመው የኤርትራ ወረራ በከፍተኛ የዜጎች መስዋእትነትና በምልዐተ ህዝቡ ርብርብ  ከተቀለበሰ በኋላ፣ አገሪቱ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖባታል። አገሪቱ የበርካታ ዜጎችን ህይወት ያሻሻለ፤ ከ50 በመቶ በላይ የነበረውን የድህነት ምጣኔ ወደ 22 በመቶ መቀነስ ያስቻለ፤ ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ የቻለችው በዚህ የሰላም ጊዜ ውስጥ ነው። የአገሪቱን የኤሌትሪክ ኃይል አቅም ከ350 ሜጋ ዋት ከአስር እጥፍ በላይ በማሳደግ 4200 ሜጋ ዋት ማድረስ የተቻለው በዚህ ሰላምና መረጋጋት ነው። አሁን በመከናወን ላይ የሚገኙትና የአገሪቱን ኢኮኖሚ በእድገት ምጣኔም ሆነ በመዋቅራዊ ሽግግር እመርታዊ ለውጥ ማምጣት ያስችላሉ ተብለው የሚታመኑ ሜጋ ፕሮጀክቶችና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ የዚህ ሰላም ወጤቶች ናቸው። በመላ አገሪቱ ሁሉንም እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ህጻናት ማስተማር ያስቻሉ ትምህርት ቤቶች፣ ቢያንስ በወረዳ ከተማ ደረጃ አንድ የሁለተኛና የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች፣

የጤና ተቋማት መገንባት የተቻለው በዚህ ሰላም ነው። አስር እንኳ የማይሞሉትን የቴክኒክና ሞያ ማሰልጠኛ ተቋማት ወደሺህ ማሳደግ የተቻለው በዚህ ሰላም ነው። ሁለት የነበሩትን ዩኒቨርሲቲች ወደ 33፣ የቅበላ አቅማቸውን ከ10 ሺህ ወደ መቶ ሺዎች ማሳደግ የተቻለው በዚህ ሰላም ነው።

አገሪቱን በተደጋጋሚ የሚመታት ድርቅ ለዜጎች እንደቅጠል መርገፍና መሰደድ ምክንያት ወደ ሆነ ችጋር እንዳይለወጥ ማድረግ ያስቻለ ኢኮኖሚ መገንባት የተቻለው ባለፋት ዓመታት በአገሪቱ በሰፈነው ሰላምና መረጋጋት ነው። ባለፈው ዓመት በሃምሳ ዓመታት አገሪቱ አይታ የማታውቀው አስከፊ ድርቅ በብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች ቢከሰትም፣ የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ፣ አንድም ሰው ከመኖሪያ ቂዬው ሳይሰደድ፣ ልጆች ከትምህርት ገበታቸው ሳይፈናቀሉ መከላከል መቻሉን ልብ በሉ።

የኤርትራን መንግስት ጨምሮ ኢትዮጵያ ደካማ ነች ብለው በገመቱበት ማንኛውም ወቅት ጥቃት ሊሰነዝሩባት የሚችሉ ስትራቴጂካዊ ጠላቶች ያሉ መሆናቸው እርግጥ ቢሆንም፤ ቅርብና ደራሽ  የወረራ ስጋት የለም። በመሆኑም በአገሪቱ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት አለ። ኢትዮጵያ ጠላቶቿ ሊያጠቋት እጃቸውን ማንሳት በማይደፍሩበት ሁኔታ ጠንካራ መከላከያ መገንባት የቻለችው ባለፋት ሁለት አስርት አመታት ገደማ በተገኘው ሰላም ጠንካራ ኢኮኖሚ በመገንባቷ ነው።

ከላይ በመጠኑ ለመግለጽ እንደተሞከረው የኢትዮጵያ ህዝብ የሰላምን ጥቅም፣  የሰላምን እጦት፤ አስከፊነትና ጉዳትም ከተሞክሮ ያውቀዋል። ይሁን እንጂ፤ አልፎ አልፎ በተለይ በከተማዎች አካባቢ የሚነሱ ለሰው ህይወት መጥፋትና ንብረት መውደም ምክንያት የሆኑ ሁከቶች አጋጥመዋል። በተለይ፤ ባለፈው ዓመት በኦሮሚያና በአማራ ክልል የተከሰተው ሁከት ሰላምና መረጋጋት ውስጥ በኖርንባቸው ሁለት አስርት አመታት ውስጥ ካጋጠሙት ሁሉ ጫን ያለው ነበር።

በህዝብ ውክልና ስልጣን ላይ ያለው መንግስትና ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በተደጋጋሚ እንደገለጹት ለሰላም መደፍረስ አመቺ የሆነው ሁኔታ የተፈጠረው በመንግስት አስፈጻሚ ተቋማት ውስጥ ባለ የመልካም አስተዳደር ችግር፣ ኪራይ ሰብሳቢነትና ኪራይ ሰብሳቢነት ባስከተለው ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል አለመኖር፤ እንዲሁም በስራ አጥነት መስፋፋት ነው። ይህ ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ ይሻሻላል ተብሎ ቢጠበቅም፣ መንግስትም አሻሽላለሁ እያለ ቃል ሲገባ ቢቆይም ይህ ሳይሆን ቀርቶ እንዲያውም በተቃራኒው እየተባባሰ ሄዶ የመረረ የህዝብ ቅሬታ የፈጠረበት ሁኔታ ታይቷል። ይህ ቅሬታ ለኳሽ አጋጣሚ ሲያገኝ አንድ ቦታ በአደባባይ ተቃውሞነት ተቀጣጥሎ በቀላሉ ተዛምቷል።

ይህ ተገቢ የሆነ የህዝብ ቅሬታ በአደባባይ ተቃውሞ መገለጹ በራሱ እንደችግር የሚታይ አይደለም። ህዝብ በመንግስት ላይ ቅሬታ ሲኖረው ወይም ጥያቄ ሲያነሳ ይህን በአደባባይ የመግለጽ ህገመንግስታዊ መብት አለው። ችግሩ ያለው ህገመንግስቱ ከፈቀደውና በአፈጻጸምም ሲሰራበት ከቆየው ተቃውሞን በሰላማዊ ሰልፍ ከመግለጽ ባፈነገጠ አውዳሚ ሁከት መገለጹ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ በመንግስት ላይ ያለውን ተቃውሞ በአደባባይ ሰልፍ የመግለጽ መብቱ ብቻ አይደለም በህገመንግስት የተረጋገጠው፤ የፈቀደውን አመለካከት፣ አቋምና ፖሊሲ የማራመድ፤ ከመሰሎቹ ጋር የመደራጀት መብትም አለው። የመንግስትን ፖሊሲና አፈጻጸም ችግሮች አጋልጦ ተጨባጭ አማራጭ በማቅረብ ለመንግስት ስልጣን የመፎካከርም መብት አለው። የተሻለ ነው ብሎ ያመነበትን ፖሊሲ ላቀረበለት አካል ድምጹን ሰጥቶ በመንግስትነት የመወከል ህገመንግስታዊ መብትም አለው።

እነዚህ ህገመንግስታዊ መብቶች በተረጋገጡበት ሁኔታ ወደ አመጽ ወይም ወደ ኃይል ትግል ለመግባት የሚያስገድድ አንዳችም ምድራዊ ምክንያት የለም።

እውነታው ይህ ቢሆንም፣ በመንግስት ላይ ቅሬታ አለን በሚል ሰበብ ህዝብ የሚጠቀምበትን የመንግስትና የግለሰቦች ንብረትና ሀብት፣ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ጭምር ያወደመ፣ ለሰዎች ህይወት መጥፋትና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቀሴን ያስተጓጎለ ሁከት ተቀስቅሷል። ይህ ሁከት ቅሬታ ባለቸው ዜጎች የተከናወነ ቢሆንም፣ ከጀርባ ሆነው ውዥንብር በመንዛት አውዳሚ ሁከቱን የጠነሰሱትና የመሩት ግን የኢትዮጵያ ስትራቴጂካዊ ጠላቶችና እነርሱ የሚጋልቧቸው በሃይል ህገመንግስታዊ ስርአቱን የመናድ ህልም ይዘው የሚባዝኑ ጽንፈኛ የዳያስፖራ ተቃዋሚዎች ናቸው። ሁከቱን በማህበራዊ ሚዲያ የመሩት በኤርትራና በግብጽ መንግስታት ስር የተለጠፉ ቡድኖች እንደነበሩ ይታወቃል። ይህንን በሁከቱ ውስጥ የተሳተፉ ግለሰቦችም አይክዱትም።

አሁን ይህ ሁከት በርዷል። በመላ አገሪቱ ሰላም ሰፍኗል። ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሁነቶች በተለመደው መንገድ እየተካሄዱ ነው። መንግስት የኢትዮጵያ ስትራቴጂካዊ ጠላቶች ፈረስ ሆነው ሁከት ወደአገራችን ውስጥ ለማስረግ በተንቃሳቀሱ ቡድኖች ውዥንብር ተደናግረው በሁከቱ ውስጥ የተሳተፉ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎችን በቁጥጥር ስር አውሎ እውነታውን እንዲገነዘቡ ያደረገ ስልጠና ሰጥቷል። የመጀመሪያ ዙር ሰልጣኞች በፈጸሙት ተግባር አዝነውና ተጸጽተው "አይደገምም!" ብለው ወደዘወትር ሰላማዊ ህይወታቸው ተመልሰዋል። በሁለተኛ ዙር ስልጠና እየወሰዱ ያሉም አሉ። እርግጥ በሁከቱ ውስጥ የሚያስከትለውን ውጤት እያወቁ ሆን ብለው የተሳተፉ ግለሰቦች ለፍርድ የሚቀርቡበት ሁኔታ እንደሚኖር መዘንጋት የለበትም።

መንግስትም በህዝብ ላይ ቅሬታ ፈጥረው የነበሩ ችግሮችን ለማቃለል የተሃድሶ ፕሮግራም ነድፎ ራሱን ለማረም እየተንቀሳቀሰ ነው። ለቅሬታ ምክንያት የሆኑ የመልካም አስተዳደር፣ የስራ አጥነት፣ የአመለካከት ብዝሃነትን ማስተናገድ የሚያስችል ሁኔታ መጥበብ ወዘተ. ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት እየሰራ ነው። በቅርቡ ተጨባጭ ለውጥ ይታያል የሚል እምነት አለ።

በአጠቃላይ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ስሜቱ በቀላሉ የሚነሳሰው ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል በመንግስት ላይ ቅሬታ ቢኖረው እንኳን ይህ እንዲስተካከል ማድረግ የሚያስችሉ ህገመንግስያዊ መንገዶች ስላሉ እነዚህን ሰላማዊ መንገዶች አቅም በፈቀደ መጠን የመጠቀም ዴሞክራሲያዊ መብትና ነጻነት ያለው መሆኑን ማወቅ አለበት። በህገመንግስት የተረጋገጠውን ዴሞክራሲያዊ መብትና ነጻነት ችላ ብለው በውጭ የሚንቀሳቀሱ በተለይ ኢትዮጵያን ለማተራመስ ስትራቴጂ ነድፈው የሚንቀሳቀሱ መንግስቶች ላይ የተለጠፉ ቡድኖች አገሪቱን ከማፍረስ ያለፈ ግብ እንደሌላቸው መገንዘብ አለበት። እነዚህ ቡድኖች ህገመንግስታዊ ስርአቱን አፍርሰው የላኪዎቻቸውን አገር የማፍረስ ተልዕኮ ከማሳካት ያለፈ የህዝብን ጥያቄ የመመለስ ፍላጎትም አቅምም እንደሌላቸው በመረዳት በውዥንብራቸው ላለመለከፍ መጠንቀቅ ከወጣቱ የሚጠበቅ አስተዋይነት ነው።